


ከቴድሮስ ሐይሌ tadyha@gmai.com

*<<ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ። ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ፥ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ። >>ማቴ.፪፡፲፫-፲፭*

*በስልጣን ፍቅር ስለ ምድራዊ ሥልጣን የሄሮድስ ጭካኔ።የእናት ጡት ያልጠገቡ፣ ንግግር የማያውቁትንና ገና በእናታቸው እቅፍ ያሉትን ሕፃናትን ሄሮድስ በግፍ አስጨረሳቸው።*

*የዋይታና የመራራ ልቅሶ ድምፅ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፤ የሉምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች። ኤር. [illegible]፡ ፲፭*

በሃገራችን የቆየ ባህል ሴቶች ህጻናትና አረጋውያን በፍርድ አደባባይ ይሁን በጦርነት ቀጠና ምርኮ የሚደርግላቸው አያያዝና የሚታዩበት ሁኔታ ልክ ያለው አክብሮት ያለበትና ሃዘኔታ የጨመረ እንደነበር ከታሪክ መዛግብት መረዳት ይቻላል፤ሴትና ሕጻን ማርኮ ይሁን አቁስሎ የሚፎክርና የሚያቅራራ ሊኖር ይቅርና ይህን አይነት ሙከራ ሊያደርግ የሞከረ እንኳ በማህበረሰቡ የመናቅና የመገለለል ሁኔታ ይደርስብት እንደነበር ከታሪክ መዛግብትመረዳት ይቻላል ።



*ሸመሃል መለስ ዜናዊ*

ባህልና ወጋችን ይሄ ሆኖ ሳለ ላለፉት ሁለት አስርዕተ አመታት ሀገረችንን ረግጦና ሕዝባችንን በጭቆና ቀንበሩ ቀፍድዶና በግድ ያለ ምርጫና ፍላጎታችን እላያችን ላይ የተጫነው የትግራዩ ነጻ አውጭ ነኝ ባዩ አረመኔ የማፍያ ቡድን ስልጣኑን ከተቆጠጠረበት ጊዜ አንስቶ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በንጹሃን ሰላማዊ ዜጎዎች ላይ በአረካና በበደኖ በግራኝ ዘመን እንኳ ያልትደረገ የዘር ማጥፋትና የሰቆቃ ተግባር የደረሰች ነፍሰ-ጡር ሴት ሆድ በሳንጃ ሲቀደድ የእንስቶች ጡት በቢላ ሲከተፍ ከነበረበት የዋይታና የጣዕር ዘመን አንስቶ በተለያዩ ግዚያት ከህጻን እስከ አዋቂ ድረስ እድሜና ጾታ ሳይለይ የተካሄደው የጭፍጨፋና የእንግልት ተግባር መቆሚያና መግቻ አጥቶ ወገን በመከራ አዙሪት ሲናጥ እዚህ ደርሰናል ።



*ስምየለሽ ኢትዮጵያ*

ሄሮድስ  በሺወች ህጻናት ላይ የፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ በስልጣን ፍቅር ከመታወሩ የተነሳ እንደ ሆነ ሁሉ የኛው መለስ ዜናዊም የዘረኝነት ስካር ናላውን ስላዞረውና የስልጣንና የጥቅም ፍላጎቱ ሕሊናውን ከመጋረዱ የተነሳ ማስተዋልና ማመዛዘን ተስኖት በ1997 ዓ/ም ድምጹን ለማስከበር በወጣው ሕዝብ ላይ የጅምላ ፍጅት እንዲካሄድ በማዘዝ በተለይም ታዳጊ ወጣቶችን በመለየት በአዲስ አበባ የተካሄደው ጭፍጨፋ ከሕሊናችን ሳይጠፋ ሌላ አሰቃቂ ድርጊት ገና አፍ ያልፈቱ ጨቅላ ሕጻናት ላይ ጭምር ማካሄዱን ቀጥሎበታል ።

ሰሞኑን ሽብርተኛ እያለ በማሰቃያ ማጎሪያው የከተተታቸው የሕዝብ አለኝታዎች የሰላምና የዲሞክራሲ ተሟጋቾች የቅርብ ወንድሞቼ በተለይ እስክንድር ነጋን ለማጥቃትና ሞራሉን ለመስበር የአምስት አመት ሕጻን ልጁ ፊት የተከናወነውን ኢ-ሠብአዊና ሕገ-አራዊት ተግባር ሕጻኑን እንዴት እንዳሳቀቀው እናቱ ጀግናዋ ጋዜጠኛ ሠርካለም ፋሲል በቅርቡ የገለጸችውን ብዙዎቻችን አንብበናል ። ልባዊ ወንድሜ  እስክንድር ነጋ  ያኔ በምርጫ 97 ማግስት ሕብረቱን በመወከል በነበረኝ የፖለቲካ ተሳትፎ ችግር እንዳይገጥመኝ በሃሳብ ያልተለየኝና በነበረኝ የውጪ ጉዞ እድል ተጠቅሜ ለግዜው ዞር እንድል በተለይ በወቅቱ ለተወለደው አራስ ልጄ በጣም የተጨነቀልኝና በብዙ መንገድ የረዳኝ ለአረጋውያንና ለሕጻናት በተለይ በጣም የተለየ እርሕራሄ የነበረው ይህ ደግና ለሰው አሳቢ ቅዱስ ሰው ላይ በልጁ ፊት የተካሄደበት አሳፋሪና አሳዛኝ ድርጊት ኢትዮጵያ ምድር ላይ የተፈጠረ ሰው ያደርገዋል ተብሎ የማይጠበቅ ፍጹም አረመኔያዊ ተግባር ነው።

በኔ ተሞክሮና ባለፍኩበት የፖለቲካና የመንፈሳዊ የህይወት ገጠመኝ በእውነት ለመመስከር እስክንድር ነጋን የማነጻጽረው በገዳም ተወስነው በምናኔ እንዳሉ ፍጹም መንፈሳዊ አባቶች ነው ፤ ይህ ሰው አውቃለሁ ብሎ የማይገበዝ ሐብት አለኝ ብሎ የማይመጻደቅ ትንሽ ትልቅ ሐብታም ደሀ የማይል በፍጹም ትህትና ሰውን የሚያከብር ፤ እግዚያብሔርን የሚፈራ በጠንካራ ግብረገብነት የታነጸ ባለ ጽኑ የሞራል ሰው ሁከትና ብጥብጥ መፍጠር ይቅርና ጮክ ብሎ የማይናገር አንደበተ ቁጥብ የሰላም ዘብ ጥልቅ የታሪክ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እውቀት ያለው ንባብ ቀለቡ የሆነ ለነዳያን የሚራራ ኪሱ ውስጥ ያለውን አራግፎ የሚሰጥ ለነገ የማይል በጣም ደግነ ሊጋስ መሆኑን ድፍን ፒያሳና አራት ኪሎ ያሉ ነዳያን ጭምር የሚመሰክሩለት ሠላማዊ ዜጋ ነው ከነቤተሰቡ እንግልትና መከራ የሚፈራረቅበት።

አበው የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ  ይላሉ ወላጅ ቢያጠፋ እንኳ ጨቅላ ሕጻን እንዴት ሕሊናው እንዲታወክ ተደርጎ ይቀጣል የዛሬዎቹ ባለ ጊዜዎች ለልጆቻቸው ለምን የቂምና የቁርሾ ውርስ ትተው ይሄዳሉ ይህን ከታሪክ ሊረዱ ይገባል የትላንቱ ባለ ጊዜ አብዮታዊው መሪ መንግስቱ ልጆቹ  በአባታቸው ተግባር በማፈራቸው አበሻ ካለበት የሚርቁና ወገናቸውን የሚሸሹ ገለልተኞች ሆነው ለመኖር እንደተገደዱ ይነገራል ።

(ብእሴ ደም ወጉህላዌ ያስቆርር እግዚያአብሔር )" ደም አፍሳሹን ሸንጋዩን ሰው እግዚያብሔር ይጸየፋል እንዲል ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ  (መዝ. 5. ቁ6)  ሐሰትን በመዝራትና ውሸትን በማምረት የንጹሐንን ደም በማፍሰስ የሚጸና ስልጣን የሚገኝም የሕይወት መደላደል ባለመኖሩ ቀን የሞላላቸው ባለ ጓንጃና ጦር ታጣቂዎቹ አሳሪና ፈቺ ከሳሽና ዳኛ ለሆኑት ለፍርደ ገምድሎቹ የሕወሐት መሪዎች በሰፈሩት ቁና መሰፈርን በተኮፈሱበት አደባባይ መዋረድን ለ20 አመታት አስረው የበቀል ጥማታቸውን ከተወጡባቸው የደርጉ አረመኔ ሹንባሾች ሊማሩ በተገባ ነበር በሕዝብ ላይ የጠለቀችው ፀሐይ

ብትዘገይም መውጣቷ አይቀርምና በእውነትና በድፍረት የሕዝብ ብሶት ገንፍሎ ከቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ በፊት በተባ ብእራቸው ለመከሩት የዲሞክራሲ ፋና ወጊ ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ላይ አፈና በማካሄድ ሊቀለበስ የማይችል በሚሊዮኖች ሕሊና የሚብላላ የለውጥ ማዕበል እያስገመገመ መሆኑን ተረድቶ ግዜው ሳይጨልም ባንዳውም ጭፍራውም ጌታውም ልቦናውን ሊያቀና በተገባ ነበር !!

በመጨረሻም ምድራዊ ያልሆነ ሰማያዊ ከሰው ያልሆነ ከእግዚያብሔር የተሾማችሁ  አይእንተ ካህናትና አበው መነኮሳት እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖት ቃዲዎችና መንፈሳዊ መሪዎች ፍትሕ ስትጠወልግ የሕግ ልዕልና ሲገሰስ ደሀ ሲበደል ፍትሕ ሲጓደል በዘረኝነት መርዝ ሕዝብ ሲበከል ሀገር ያሉ ለወገን በተቆረቆሩ ለግላጋ ወጣቶች በግፍ ሲጋዙ አረጋውያን ሲንገላቱ ሕጻናት ላይ የሕሊና ሰቆቃ ሲፈጸም ወገን ተርቦ በችጋር ሲወድቅ ከቶስ ድምጻችሁ አይሰማ ቃላት በማስረዘምና በሞቀበት መኩነስነስ ከተበዳይ ሳይሆነ ከበዳይ ጋር መቆም ነው እንዴ መንፈሳዊነት ለነገሩ የውድቀታችን ሁሉ መሠረት መንፈሳዊ ተቋማት የተደፈሩ እለትና መንፈሳዊ ነን ባይ አባቶች ከወንጀለኞች ጋር እየተሞዳሞዱ የሞራል አዘቅት ውስጥ ከወደቁ በኋላ ነው ።

ያም ሆኖ በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ መጽሐፉ እንዲል ታላቋ ሀገራችን ቅድስቲቱ ኢትዮጵያ ወላድ በድባብ ትሂድና ለነጻነቷ የሚቆረቆሩ ለወገናቸው መብት ቤዛ ለመሆን የቆረጡ  እስከንድር ነጋን አንዷለም አራጌን ፍሬሕይወት አለሙን ውብሸት ታዬ የመሳሰሉተና ሌሎች ስማቸው ያልተጠቀሱ የሰላም ተጋዮች ከነቤተሰባቸው እየከፈሉት ያለውን መስዋዕትነት ለሁላችን የሚጠቅም መብትና ነጻነት እንዲሰፍን መሆኑን በመረዳት ሁላችንም በምንችለውና ባለን አቅም ለዚህ የተቀደሰ አላማ ልንቆም ይገባናል ለፍትህ መቆም ለነጻነት መታገል ፖለቲካዊ መንገድ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ግዴታ ጭምርም መሆኑን ቅዱሳን መጻሕፍትም ይገልጻሉ ለዚህም ነበር ቀደምት አባቶቻችን ግንባራቸውን ሳያጥፉ በጀግንነተ መስውዕትነትን በመክፈል ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው ነጻነት ቤዛ ሲሆኑ ሞታቸው የቅድስና ሞት መሆኑን በማመናቸው ነው ሲዋደቁ ኖረው ነው የነጻነት ታሪክ ያወረሱን።

እግዚያብሔር ኢትዮጵያችንን ይማርልን !!!   አሜን!!!